


*አስቸኳይ ከገበያ መልሶ የመሰብሰብ ጥሪ:* Abbott ለ **Similac የዱቄት** ህጻናት የዱቄት ወተቶቻቸው ከገበያ ተመልሰው እንዲሰበሰቡ ትእዛዝ ሰጥተዋል።

- Similac ዱቄት - Advance፣ Total Comfort፣ Sensitive እና Spit Up
- Alimentum ዱቄት

**ከገበያ የሚሰበሰቡ የህጻናት የዱቄት ወተቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ**:

- መለያ ቁጥራቸው ከ 22-37 የሚጀምሩ፤ **እና**
- K8፣ SH፣ ወይም Z2 (ምስሉን ይመልከቱ)፣ **እንዲሁም**
- የማብቂያ ቀናቸው ኤፕሪል 2022 ወይም ከዚያ በኋላ ያለ።

የዱቄት ወተት መለያ ቁጥሮችን በ [similacrecall.com](similacrecall.com) ያረጋግጡ።

- ከገበያ ላይ እንዲሰበሰብ የታዘዘ ከሆነ የዱቄት ወተቱን ለልጅዎ አይመግቡ።
- ሁሉም እንዲሰበሰብ የታዘዙ ጣሳዎች ላይ “Do Not Use” ("አትጠቀም") የሚል ምልክት ያድርጉ። የህጻናትን የዱቄት ወተት እንዴት እንደሚቀይሩ ወይም እንደሚተኩ ዝርዝሮችን ከዚህ በታች ይመልከቱ።

**WIC የዱቄት ወተት አማራጮች፡-**

- **[ለህጻናት የዱቄት ወተት ጊዜያዊ ምርጫዎች – ከፎቶዎች ጋር የተሰጠ ጽሑፍ (3/10/22) (PDF)]()**

**በቤትዎ ያከማቹትን እንዲሰበሰብ የታዘዘውን የህጻናት የዱቄት ወተት እንዴት እንደሚለውጡ፡-**

1. **መደብሮች** - የህጻናት ዱቄት ወተቱን ወደ መደብሩ ለመመለስ ይሞክሩ
    - እያንዳንዱ መደብር እንደሚያቀርበው ነገር የተለያየ ነው።
    - አንዳንድ መደብሮች እንዲመለስ የታዘዘውን የህጻናት ዱቄት ወተት መልሰው ወስደው ልውውጥ፣ የስቶር ክሬዲት ሊሰጡ ወይም ገንዘብ ተመላሽ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህ አማራጭ ካልዎት

ማንኛውንም የህፃናት የዱቄት ወተት ለመግዛት ያንን ክሬዲት ወይም ተመላሽ የተደረገ ገንዘብ መጠቀም ይችላሉ።

- መደብሩ የህጻናት ዱቄት ወተቱን የማይለውጥ ከሆነ ከዚህ በታች ቁጥር 2 እና 3 ይመልከቱ።

2. **Similac የዱቄት ወተት ኩባንያ (Abbott)** - እንዲሰበሰብ የታዘዘ የህጻናት ዱቄት ወተትን ወደ Abbott ይመልሱ

   ቤተሰቦች በቤት ውስጥ የተከማቸውን ተመላሽ የህጻናት ፎርሙላ ወደ Abbott መመለስ ይችላሉ። ይህን ለማድረግ፦

   - ወደ www.SimilacRecall.com ይሂዱ ወይም በዚህ ይደውሉ፦ 1-800-986-8540
   - በድረ ገፁ ላይ ወደ ገፁ ግርጌ ይውረዱ እና “Check Lot Number” ("የመለያ ቁጥሩን ይመልከቱ") የሚለው ላይ ጠቅ ያድርጉ፤
   - በተመላሽ የዱቄት ወተት ጣሳው ስር ያለውን የመለያ ቁጥር ያስገቡ፤
   - ተመላሽ የሚደረግ የህጻናት ዱቄት ወተት ከሆነ የመለያ ቁጥሩ ተመላሽ የሚደረገው ወተት አካል መሆኑን የሚገልጽ ወደታች የሚዘረዝር ፎርም ይታያል፤
   - ፎርሙን ሞልተው ይጨርሱ እና ያስገቡ፤
   - “Abbott received the return request and to watch your email for a link to get the unique return label” ("Abbott የመመለሻ ጥያቄውን ተቀብሏል እና ልዩ የመመለሻ መለያውን ለማግኘት አገናኝ በኢሜይልዎ ውስጥ ያገኛሉ") የሚል መልእክት ይታያል፤
   - ቤተሰቦች የህጻናቱን ፎርሙላ በካርቶን ውስጥ አድርገው፣ የተሰጣቸውን መለያ በማከል እና በኢሜል ላይ እንደታዘዘው ይዘው ወደ Abbott እንዲመለሱ ማድረግ አለባቸው፤
   - ቤተሰቦች ቼክ እስኪደርሳቸው እስከ 4 ሳምንታት ይወስዳል። ቤተሰቦች በገንዘቡ ሊያደርጉ የሚችሏቸው ነገሮች የተገደቡ አይደሉም።

## የWIC የህፃናት የዱቄት ወተት ጥቅማጥቅሞችን እንዴት መተካት ወይም መለወጥ እንደሚቻል፦

1. **WIC ክሊኒክ** - የህጻናት ዱቄት ወተት ጥቅማጥቅሞችን ለመተካት ወይም የህጻናት የዱቄት ወተት ለመቀየር ወደ WIC ክሊኒክዎ ይደውሉ።

   - በመደብሮችዎ ውስጥ ምን የ Women, Infants, and Children (WIC፣ ሴቶች፣ ጨቅላዎች፣ እና ሕጻናት) የህጻናት ዱቄት ወተት እንደሚገኝ ይመልከቱ;
   - እንደ አስፈላጊነቱ የህጻናት ዱቄት ወተት ጥቅማጥቅሞችን ለመተካት ወይም ለመለወጥ ወደ ክሊኒኩ ይደውሉ፤

2. **WIC ስቴት ቢሮ** - ክሊኒክዎን ማግኘት ካልቻሉ፣ ለስቴቱ በ 1-800-841-1410 ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 8 ሰዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት ይደውሉ።

## የመረጃ ምንጮች፦

- የመሠረታዊ ምግብ ፕሮግራም (Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP፣ የተጨማሪ ስነ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም)) እና የምግብ ባንኮች - **ParentHelp123 ድረገፅ** ወይም በ 1-800-322-2588 ይደውሉ።
  - ይህ ተቋም ለሁሉም እኩል እድል አቅራቢ ነው።

**ዋሺንግተን WIC መድልዎ አያደርግም።**

ይህንን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-841-1410 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ WIC@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።

DOH 961-1265 March 2022 Amharic

Washington State Department of Health